ኤቨረስት ዩዝ አካዳሚ

አማርኛ ማስታወሻ

ለ12ኛ ክፍል

ሥነ - ጽሑፍ

- ጽሑፍ ከንግግር ዘግየት ብሎ የመጣ በሰው ልጅ የስልጣኔ እድገት የተገኘ የንግግር ወኪሉ ነው :: ሰው የድምጽ ምልክቶችን በፊደል በመወከል ሀሳቡን የሚገልጽበት መሳሪያው ነው ::
- ሥነ ጽሑፍ ቃሉ እንደሚያመለክተው ሥን ማለት ውበት ማለት ሲሆን ሥነ ጽሑፍ ደግሞ የጽሑፍ ውበት ማለት ይሆናል ::
- ሥነ ጽሑፍ የቃላት አጠቃቀምን ፣ የሓሳብ ጥልቀትን የሚጠይቅና ምርምራዊ ይዘት ያለው ስሜትን በሚገነባ ሁኔታ የሚዘጋጅ ነው ::
- ሥነ ጽሑፍ በስድ ንባብ ወይም በግጥም ሊጻፍ ይችላል ::

ሥነ - ግጥም

ግጥም ማለት የስንኞችን መዳረሻ ሆሄዎች ቤት እያስመቱ ማናገር ማለት ነዉ:: ግጥም ከስድ ንባብ ይለያል:: ስድ ንባብ ዘርዘራ ነዉ:: ግጥም ከቦታ ፣ ከቅርፅ ጠባብና ዉሱን በመሆን ብዙዉን ጊዜ በተጨመቀ ሀሳብ ፣ በገነፈለ ስሜት በምርጥ ቃላት ላይ ያተኩራል:: ግጥም በምጣኔዉ በሃሳብና በስሜት ድድርነቱ የተነሳ ከስድ ንባብ ፅሁፍ ይለያል::

ግጥም ሰዉ እንደ ብረር ብረር ፣ ዝለል ዝለል ሲያሰኝ ወይም ሰዉ በንዴት ሲበግን ፣ በሀዘን ሲጥለቀለቅ፣ በሀሳብ ሲመጥቅ ነዉ ግጥም በአዕምሮ ዉስጥ መፀነሱን የምናዉቀዉ::

ግጥም ዓይነት አለዉ:: ግጥም ምንም ጥልቀትና ምጥቀት የሌለዉ ከስሜት ያልመነጨ ፣ ስሜትን የማይኮረኩር ፣ የማይነካ ፣ ግጥም አለ:: ሌላዉ ደግሞ ዉብ የሆነ ከስሜት መንጭቶ ስሜትን የሚነካ ጊዜ ድንበር የማያግደዉ በየትኛዉም ቦታና ሕዝብ ፊት ቢነበብ ዘላቂነት ፣ ተቀባይነት ያለዉ ግጥም አለ:: የዚህም አይነት ግጥም ሥነ- ግጥም ወይም ዉብ ግጥም ይባላል::

ዉብ ግጥም ጣዕም አለዉ:: የሃሳብ ምርጫዉ ፣ የስሜት ንዝርቱ ፣ ጥራቱ ፣ ግለቱ ፣ መንተግተጉ ፣ አዲስነቱ ፣ የቋንቋዉ ጥራትና ምጥቀቱ ፣ ቀላልነቱ የሐረጋቱ ምጣኔ ዜማዊነቱ ፣ ትኩስነቱ ፣ በአጠቃላይ በቅርፁ፣ በይዘቱ ዉበትን የተላበሰ ነዉ:: በአማርኛ ቋንቋ ሥነ - ፅሁፍ ታሪክ ዉስጥ ግጥምና ስነ - ግጥም ግንባር ቀደም እንደነበሩ ይነገራል:: እስካሁን የተገኙት የግጥም ቅርሶችም ይህንኑ ያረጋግጣሉ:: ለምሳሌ እንደ ኢትዮ. አቆጣጠር ከ 1314 — 1344 ዓ.ም ለነገሱት ለአፄ አምደ ፅዮን እና ከ 1382 — 1411 ዓ.ም ድረስ ለነገሱት ለአፄ ዳዊት እንዲሁም ከ1414 — 1429 ዓ.ም በዙፋን ላይ ለነበሩት ለአፄ ይስሀቅ የተገጠሙ ሶስት ግጥሞች ተገኝተዋል:: ይሁንና ከአስራ አራተኛዉ ምዕተ ዓመት በፊት በስድ ንባብ መልክ የተደረሱ ፅሁፎች የሉም ብሎ መደምደም አይቻልም::

ግጥምና ስነ - ግጥም የሚሉትን እሳቤዎች ማምታታት አይገባም፡፡ ስነ - ግጥም የግጥም አፃፃፍ ጥበብ ማለት ነዉ፡፡ በሌላ አገላለፅ ግጥምን ዕዉን ለማድረግ የሚኖረዉን ስንክናዊ የአበጃጀት ተግባርና ግጥምን ምልዓት እና ተፈጥሮ የሚያካትት የስነ - ፅሁፍ ዘርፍ ነዉ፡፡ ስነ- ግጥም የጥበቡ መጠሪያ ነዉ፡፡
ግጥም ደግሞ የጥበቡ ዉጤት መጠሪያ ነዉ፡፡በስንኞች የሚመጠን ምትናዜማ ያለዉ፣ቤት የሚመታ፣በዚህም በስድፅሁፍ የሚለይ መልዕክትን፣ ለዛ፣እምቅነትናከረት፣ባለዉ መልኩ ለመግለፅ ወይም ለማስተላለፍ የሚያስችል ኪናዊ የሃሳብና የስሜት መግለጫ ነዉ፡፡

<u>የግጥም የቃላት ምርጫ አቅጣጫዎች</u>

ሀ. ቃላተ - ምሁር፡- ከሰርካዊ ቃላት ዉጪ በአብዛኛዉ በተማሩ ሰዎች ዘንድ የሚታወቁ ወይም ከአንድ የተለየ ሙያ ጋር የተያያዙ ቃላት ናቸዉ፡፡

ለ. ድምፀ - ቀድ ቃላት፡- አንድን ነገር ድርጊት ወይም እንቅስቃሴ በመቅዳት ይፈጠራል፡፡ ለምሳሌ እንደ ቀረርቶ፣ ቻቻታ ፣ ጉርምርምታ ወዘተ ....

ሐ. ወለለት ቃላት፡- ስሜት ከነ ሙዚቃ ቃናዉ እንዲገኝ ለማድረግ የሚመረጡ ሲሆኑ የቃላቱን መድረሻ ድምፆች አከታትሎ የሚከሰቱ ናቸዉ፡፡

መ. ቃላት - ፈጠራ፡- ገጣሚያን ፈልገዉት ቃላትን ፈጥረዉ ሲፅፉ ይታያል፡፡ ይኸዉም የተለየ ገላጭነት ፣ ሙዚቃዊነትና ግብ መቺነት ይኖራቸዋል ብለዉ የሚያምኑባቸዉን ቃላት በመፍጠር ሃሳባቸዉን ይገልፃሉ፡፡ እንዲህ ያሉትን ቃላት በስነ - ግጥም ዉስጥ ማስገባት የተከለከለ አይደለም፡፡ ነገር ግን የተፈጠሩት ቃላት በደራሲዉና በአንባቢዉ መካከል ሊኖር የሚገባዉን ኪነ - ጥበባዊ መግባባት እንዳያግዱት መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የሚፈጠሩት ቃላት የቋንቋዉን ቃላት አፈጣጠር ስርአት የጠበቁ ፣ ተገቢዉን ቅርፅና ድምፅ የያዙ መሆናቸዉን ገጣሚዉ ማስተዋል አለበት፡፡

ምሳሌ፡- ሱርት፣ጥቁርት፣ጭምትወዘተ

በአማርኛ ቋንቋ ስነ - ግጥም አሰኛኘት

በአማርኛ ቋንቋ ዉስጥ ሶስት የተለመዱና በተደጋጋሚ የሚሰራባቸዉ አሰኛኘት ዓይነቶች አሉ፡፡

ሀ.የወልቤት፡- ከሁሉም በይበልጥ ስራ ላይ የሚዉሉ፣በቀለም፣ በብዛትም የበላይነት ሀረጋቱ ዘለግ ዘለግ ያሉ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- አመለ ሽጋዋ / የናቴ ልጅ እቴ
ፈጥና ትደርሳለች / ስቸገር ከቤቴ፡፡
የተስተካከሉ ስንኞች በሀረግ 6 በስንኝ 12 ቀለማት አሉት፡፡
ለ. የሰንጎ መገን ቤት፡- ከወል አጠር ያለ ፣ የፉከራ ድምፅ ያለዉ ፣ በቀለምም በሀረግም አምስት በስንኝ ደግሞ አስር የሆነ ግጥም ነዉ፡፡
ምሳሌ፡- ዉረድ እንዉረድ / ተባባሉና
አስደበደቡት / አፋፍ ቆሙና፡፡
ሐ. የቡሄ በሉ ቤት፡- ከሁሉም አጠር አጠር ያሉ ስንኞች ያሉት ሲሆን በቀለም ብዛት በሀረግ አራት በስንኝ ደግሞ ስምንት ቀለማት አሉት፡፡
ምሳሌ፡- እግረ ቀጭን / እንደ ሰሳ
ልበሙሉ / እንዳንበሳ

ግጥምን ወደ ዝርዉ መለወጥ (ceuter)

➢ በግጥም የተፃፉትን (የተፃፈን) መልዕክት ወደ ዝርዉ በመለወጥ ዋናዉን ሃሳብ ሳያዛቡ ለአንባቢ ማቅረብ ይቻላል፡፡

ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉትን ደረጃዎች መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

1. ግጥሙ የያዘዉን መልዕክት ለመረዳት ደጋግሞ ማንበብ
2. የግጥሙን ፍሬ ሀሳቦች እየለዩ በማስታወሻ መመዝገብ
3. በማስታወሻ የተያዙትን ፍሬ ሀሳቦች በመጠቀም ግጥሙን ወደ ዝርዉ መለወጥ የሚያስችል አስተዋፅኦ መንደፍ፡፡
4. ዋና ዋና ንዑሳን ሀሳቦች ለይቶ ማስቀመጥ
5. መንደርደሪያ ዐ.ነገሮችንና ዝርዝር ዐ.ነገሮችን ማዋቀር
6. ፅሁፉ ሀሳብ አንድነት ይኖረዉ ዘንድ የአንቀፆችንና በየአንቀፆቹ የሚገኙ ዐ.ነገሮች ተያያዥነታችነታቸውን መጠበቅ፤ይህንንም በሁለት መንገዶች መጠቀም ይቻላል፡፡

ሀ. በሃሳብ እንዲያያዙ ማድረግ፤
ለ. በአያያዥ ቃላት እንዲያያዙ ማድረግ፤

፯ እንደ አስፈላጊነቱ የግጥሙን መልዕክት የያዙ ስንኞችን በማስረጃነት መጥቀስ
፰ ፅሁፉ ካለቀ በኋላ የተፃፈዉን ረቂቅ ደጋግሞ በማንበብ ማስተካከያ መስጠት

፱ ግልፅ እና ቀላል ቋንቋ በመጠቀም አንድን በግጥም መልክ የተፃፈን ሃሳብ ይዘቱን ጠብቀን ወደ ዝርዉ ፅሁፍ መለወጥ እንችላለን፡፡

የቃለ መጠይቅ ዝግጅትና አቀራረብ

- ቃለ መጠይቅ ፍሬ ሀሳቦችን ለማግኘት ወይም ለመሰብሰብ ፣ አሳምኖ ለማስፈፀም ፣ ሰራተኛን ለመቅጠር ፣ ትምህርት ለመከታተል ፣ ጥናታዊ ምርምር ለማካሄድ ወዘተ . የሚቀርብና መልስ የሚሰጥበት የቃል ጥያቄ ነዉ፡፡ ይህንንም ለመተግበር የቅድመ ዝግጅት ጊዜ ቃለ መጠይቅ ስርአቶች አሉ፡፡

፩. ቅድመ ዝግጅት፡- በዚህ ወቅት የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ዉስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

ሀ. ጥያቄዎችን በቅድሚያ ማዘጋጀት

ለ. ለቃለ መጠይቁ ቀደም ብሎ ቀጠሮ መያዝ ፤ ቀጠሮ ለመያዝ በሚከተሉት መንገዶች መጠቀም ይቻላል፡፡

- ደብዳቤ በመፃፍ
- በቴሌፎን ጥሪ
- በግንባር መነጋገር

ሐ. ቦታዉን ፣ ቀንና ሰዓቱን ተጠያቂዉ እንዲወስን ማድረግ

መ. የቀጠሮን ሰዓት ማክበር

፪. ቃለ መጠይቅ በሚቀርብበት ጊዜ ልንከተላቸዉ የሚገቡ ስልቶች

ሀ. ለተጠያቂዉ ራስን በስርአቱ ማስተዋወቅ

ለ. ጥያቄዎቹ ግልፅና ቀጥተኛ እንዲሆኑ ማድረግ

ሐ. በምንጠይቅበት ወቅት ትሁትና ቁም ነገረኛ መሆን

መ. ጥያቄዎችን እያቀረቡ በጥሞና ማዳመጥ

ሠ. ዋና ቃል ሐሳቦችን መያዝ

ረ. በመጨረሻም ተጠያቂዉን ማመስገንና ጠቅላላ ዘገባዉን ፅፎ በማቅረብ በአግባቡ የተደራጀና ቃለ መጠይቅ ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡

የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ

- ክርክር ሁለት ተቃራኒ ሃሳቦች በሁለት ሰዎች ወይም በሁለት ቡድኖች መካከል በተሰየሙ ዳኞች ፊት የሚደረግ ስርዓት ያለዉ ሙግት ነዉ፡፡

- ክርክር ለማካሄድ ቅድመ ዝግጅት የሚያስፈልግ ሲሆን በክርክር ወቅትም ልንከተለዉ የሚገባ ህግና ስርአት አለ፡፡

ሀ. የክርክር ዝግጅት

፩. ርዕሱን በሚመለከት ከተለያዩ ምንጮች ሃሳብ መሰብሰብ ፤ ለምሳሌ፡-

- ከባለሙያዎች
- ከልዩ ልዩ የስነ ፅሁፍ ዉጤቶች

፪. በርዕሱ መሰረት ጠይቀን ካገኘነዉና ካነበብነዉ ለክርክሩ ጠቃሚ የሆኑትን ሃሳቦች በቅደም ተከተል አስተካክሎ መያዝ
፫. ክርክሩን ከማቅረብ በፊት በቂ ልምምድ ማድረግ
፬. ለክርክሩ ከመቅረብ በፊት ስብዕናችንን በስርዓት ማሟላት

ለ. የክርክር አቀራረብ

፩. የመከራከሪያ ርዕስን ለታዳሚያን ማቅረብና ማስተዋወቅ
፪. የክርክራችንን ፍሬ ሀሳብ በቅደም ተከተል ማቅረብ
፫. በክርክር ወቅት ረጋ ባለ መንፈስ ፤ በልበ ሙሉነት ማቅረብ
፬. ከክርክሩ ጋር የማይስማማ እንቅስቃሴ አለማድረግ
፭. ተቋዋሚ አካላት የሚሰጠዉን ሃሳብ በትክክል በማዳመጥ ማስታወሻም በመያዝ የተቃዉሞ ሀሳብ ማዘጋጀት
፮.ማስታወሻ መያዛችን በትክክል በተቃራኒ አካላት ዘንድ እንዳይታወቅ ማድረግ
፯. የሚቀርበዉ ሃሳብ ወይም ማስረጃ በአድማጮች ችሎታ የተመጠነ እንዲሆን ማድረግ
፲.ለክርክሩ የተሰጠዉን የጊዜ ገደብ ማክበር ወዘተ የተዋጣ ክርክር ለማከናወን የሚያስችሉ ስልቶች ናቸዉ፡፡

የዋቢ ጽሑፎች የአደራደር ሥርዓት

የተለየዩ መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች አገላብጠን ያገኘነዉን መረጃ በፅሁፋችን ከተጠቀምን በኋላ በፅሁፋችን መጨረሻ ገፆች"ዋቢ ፅሁፎች" በሚል ርዕስ ስር በፊደል ተራ ቅደም ተከተል የመረጃ ምንጮቻችንን በስርዓት መደርደር ያስፈልጋል፡፡

- የተለያዩ የአደራደር ስርዓቶች ሲኖሩ በቋንቋ ዘርፍ የሚዘወተርን ስርዓት ወስደን በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ መፃህፍት እንዴት እንደሚሰፍሩ እንመለከታለን፡፡በዚህ መሰረት አንድ መፅሃፍ በዋቢነት ሲሰፍር በቅደም ተከተል መደርደር ያለባቸው መፅሃፉን የተመለከቱ መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

የደራሲዉ ስም ፣ የታተመበት ዓመት ምህረት (በቅንፍ ዉስጥ ገብቶ) ፣ የመፅሀፉ ርዕስ / ከስሩ ከተሰመረበተ ወይም ኢታሊክ ከሆነ በኋላ አራት ነጥብ አርፎበት/ ፣ የታተመበት ቦታ /ነጠላ ሰረዝ አርፎበት/ በቅደም ተከተል ወደ ጎን ይደረደራል፡፡

ምሳሌ 1፡- ፈቃደ አዘዘ (1995) የስነ - ቃል መመሪያ፡፡ አዲስ አበባ ፣ ኢትዮ ጥቁር አባይ አሳታሚዎች፡፡
የተጠቀምናቸዉ መፃህፍት ሲዘረዘሩ ቅደም ተከተላቸዉ የሚወሰነዉ በደራሲዉ ስም ፊደል ተራ ይሆናል፡፡የደራሲዉ ስም ባልተጠቀሰ ጊዜ ደግሞ የመፅሀፉ ርዕስ ፊደል ተራ ለአደራደሩ መሪ ይሆናል፡፡በሌላ በኩል አንዳንድ ጊዜ አንድ መፅሀፍ ከአንድ በላይ ደራሲ ሊኖረዉ ይችላል፡፡ እንዲህ ያለዉ ሲያጋጥም እስከ ሶስት የሚደርሱ ከሆነ (እገሌ ፣ እገሌና እገሌ) በማለት ፣ ከሶስት በላይ ሲሆኑ ደግሞ መጀመሪያ ላይ ያለዉደራሲ ስም ተወስዶ /እገሌ እና ሌሎች/ ተብሎ ይሰፍራል፡፡

ምሳሌ 2፡- ሀ. መስፍን ሀብተ ማርያም እና ሌሎች (1977) አባ ደፋርና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች፡፡ አዲስአበባ ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ለ. አምሳሉ አክሊሉ እና ዳኛቸዉ ወርቁ (1983) የአማርኛ ፈሊጦች፡፡ አዲስ አበባ ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

- በፅሁፋችን ዉስጥ በአንድ ደራሲ የተፃፉ ሁለትና በላይ መፃህፍትን አግኝተን ስንጠቀም በመጀመሪያበምሳሌ 2 መሰረት በፊደል ተራ ከዘረዘርን በኋላ ፣ ሁለተኛዉ መፅሀፍ በደራሲዉ ስም ትክክል ዳሽምልክት (_) ይደረግና የቀረዉ በስርዓት ይደረደራል፡፡

ምሳሌ 3፡- ዳኛቸዉ ወርቁ (1962) አደፍርስ፡፡ አዲስ አበባ ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡
------------------ (1977) የፅሁፍ ጥበብ መመሪያ፡፡ አዲስ አበባ ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ጥያቄዎች

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ፡፡

1. በግጥምና በስነ -ግጥም መካከል ያለውን ልዩነት ዘርዝራችሁ ፃፉ ፡፡
2. ስነ-ፅሁፍ ምንድን ነው?
3. በግጥም የቃላት ምርጫ "ወለለት ቃላት" ምንን የሚያመለክት ነው?
4. ግጥምን ወደ ዝርዉ ለመለወጥ ከሚያስችሉ መመሪያዎች ውስጥ ሶስቱን መርጣችሁ አበራሩ፡፡
5. ቃለ መጠይቅ በሚቀርብበት ጊዜ ልንከተላቸው ከሚገቡ ስልቶች ሁለቱን መርጣችሁ አብራሩ፡፡
6. በክርክርና በውይይት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ዘርዝራችሁ ፃፉ፡፡
7. ዋቢ ፅሑፍ ምንድን ነው?
8. በአማርኛ ቋነቋ ዋቢ ፅሑፍ እንዴት እነደሚሰፍሩ በዝርዝር ፃፉ፡፡